የካቲት ፲፯ ቀን ፪ ሺህ ፪ ዓ.ም

# ምርጫው ተአማኒነት እንዲኖረው እንረዳዳበት?!

ለጠ.ሚ. መለስ                                   የገዥው ቡድን መሪ
በለንደን ኤምባሲ በኩል
ለፕሮፌሰር መርጋ በቃና                                  የምርጫ ቦርድ ሃላፊ
በለንደን ኤምባሲ በኩል
ለተቃዋሚ ቡድኖች መሪዎች                    በየአንባቢያን ደጋፊዎቻቸው በኩል
የየሃይማኖቶች መሪዎች                        በተከታታያቸው በኩል
በውጭም በውስጥም ላላችሁት ኢትዮጵያውያን    በያላችሁበት

መግቢያ፡-

ኢትዮጵያ በሕዝብ ፈቃድ (ዴሞክራሲ) ትተዳደራለች ከተባልንና በሕዝብ ነጻ ምርጫ ገዥዎቿን ትመርጣለች ተብሎ ከተለፈፈልን አያሌ ዘመናት አልፈዋል። መርዘሙንም ኾነ ማጠሩን በታሪክ ልግለጸው?

በአጼ ምኒልክ ዘመን አሊ ቦሩ የሚባሉ ደግ ስመ-ጥር በወሎ ውስጥ የአምባሰል ባላባት / ገዢ ነበሩ። ከዕለታት አንድ ቀን በማለዳ የነጋሪት ጉሰማ ይቀሰቅሳቸዋል። አጋፋሪያቸውን ጠርተው “ምን መጣ? ለምን ነጋሪት ተጎሰመ?” ብለው ጠየቁ።

አጋፋሪውም ለሳቅ በተጠጋ ፈገግታና ፍንደቃ “ ጌታዬ፡- ዛሬ እኮ ሥልጣን ከያዙ…ዓመት ነው! ” ሲላቸው

ታላቁ መሪ ለሃዘን በቀረበ ተምስጦ ሲተክዙ፡- አጋፋሪው ደንግጦ “ምነው ጌታዬ፡- ያልኹት እኮ ሥልጣን አልጋዎ ላይ ከወጡ … ዓመት ነው፡- ነው ያልኹት” አለ (እንደዚያ የተደመሙት ከሥልጣን ወረዱ ያልኳቸው መስሏቸው ይኾን? በማለት)

እኛ በፈሪሃ እግዚአብሔር የኖሩ አባት የአጋፋሪያቸውን ድንጋጤ በማየት፡- “ያልከውን ሰምቻለሁ። ግን ለሚወድደንስ ይኹን ለሚጠላን ምን ያኽል ከብደነው ይኾን?” አሉ። የሚሰማ ጆሮ ያለው ይስማ!!

ገዥዎቹ ለ 'አራተኛ' ምርጫ ይላሉ። ተቃዋሚዎቹና ብዙሃኑ ግን ለአራተኛ ስመ-ምርጫ ማለታቸውን የማያውቀው የለም። ገዥዎቹ ጭምር።ለረጅም ጊዜ ጠ. ሚንስትሩ ከ፳፱ ሺህ በላይ ማሕበሮች ያሉትን የወጣቶች

ማሕበር ወኪሎች (ለሦስት ጊዜ ከ፬ሺህ በላይ አባላትን) እንዲሁም የመምሕራንንና የሠራተኛን ሌሎችንም ማሕበሮች እየሰበሰቡ፦ የምርጫ ቿ፯ቱ ነገር እንዳይደገም፦ የሚቀጥለው ምርጫ በሕገ-መንግሥቱ ( አፍ ቢኖረው ምነው ባልተፈጥርኩ ባለ ነበር ይኼ ሕገ-መንግሥት ተብዬው)መሠረት መኾን አለበት፦ እያሉ መወትወታቸውን ሬዲዎናቸውንና ቴሌቪዥናቸውን የሚከታተል ኹሉ ሊመሰክርላቸው ይችላል!

ይኸንንም ለማሳካት ብዙ ያነጋገረውንና ያወዛገበውን " የምርጫ ሥነ-ሥር ዐት ...ን" ያስታውሷል። ወደድንም ጠላን ምርጫው ለጊዜው አይቀሬ ይመስላል ፦ እደግማለሁ ይመስላል። ይኸን ለማረጋገጥ ግን በ " እንረዳዳ..." መልክ የቀረበውን የተረሳውን ቁምነገርና ዓቢይ የምርጫ መስፈርት ማሟላት መጥቀሙ አያነጋግርም።

ጠ.ሚሩ ኤርትራን ...በኋላ አሥመራ ሄደው ' ከእናንተ በመወለዴ/ በመፈጥሬ እኮራለሁ! ' ካሉ በኋላ " ቁስላችሁን አትከኩት" ያሉትን/የሰጡትን ምክር በማስታወስ፦ባለፈው ምርጫ በአንድ ድሃ፦ ግን ቆራጥ ገበሬ ወገናችን ላይ የደረሰውን በመጥቀስ መግቢያዬን እዘጋለሁ።

አንድ ከአውሮፓ ወደ አገሩ የሚመለስ ሰው የይለፉን ለማሳየት መጓጓዣ ሰነዱን (ፓስፖርቱን) ሲያወጣ ከኋላ ያለው ነጭ የኢትዮጵያዊው ሰነድ የኢጣሊያን መኾኑን ሲያይ ደስ ይለውና

- ፈረንጅ፦ 'እባክህ የኔን ይለፍ እስከማስመታ፤- አትቸኩል እንደኾን ቆየኝ' ይለዋል
- ኢትዮጵያዊው፦ ' አልቸኩልም፡ እጠብቅሃለሁ
- ፈረንጅ ' የያዝኸውን መጓጓዥያ ሰነድ ትወድደዋለህ?'
- ኢትዮጵያዊው ' አዎን።'
- ፈረንጅ ' እንዴት አገኘኸው?'
- ኢትዮጵያዊ ' በአባቴ ጣሊያናዊ ስለኾንኹ'
- ፈረንጅ ' ከዚህ ክፉ/ጨካኝ ሕዝብ ትወለዳለህ?' ብሎ ፊቱ ኹሉ ይቀላል። እንደመንቀጥቀጥም ያደርገዋል፡
- ኢትዮጵያዊው ንዴቱን ላለማሳየት እየታገለ የፈረንጁም ኹናቴ እያሳሰበው፦ 'ለምን እንዲህ አልህ? ለምንስ ፊትህ ኹሉ ተለዋወጠ?' ሲለው ፈረንጁ አፈር/ደንገጥ ብሎ፡

- ፈረንጁ ‘ ይቅርታ! ስሜቴን እንዲህ አሳየሁ እንዴ? ያን ጭካኔ ካየሁ ወዲህ ሳስበው ይዘገንነኛል።

ያስጨንቀኛል። በዚህም ምክንያት የሥነ-ልቦና ሐኪም ማየት ነበረብኝ። ታላቅ ይቅርታ! ይህ አነጋገርና ኹንቴ ከንክኖት

- ኢትዮጵያዊው ‘ ምን አየህ? ኢትዮጵያ ውስጥ?’
- ጣሊልያን ‘ ባለፈው ምርጫ ከአውሮፓ የምርጫ ታዛቢዎች ውስጥ አንዱ ነበርኩ። የምርጫው ዕለት (ቦታውን ልተወው - ቁስልን ላለማሳከክ) አንድ ሰው ወደ መምረጫው ጣቢያ ሲቃረብ አንድ ሰው ድምጽ መስጫህን ወረቀት ስጠኝ ይለዋል። አልሰጥም - ስጠኝ! ሲባባሉ ስጠኝ ባዩ ሽጉጥ ያወጣና ግምባሩ ላይ አፈላበት። ብሎ እንደመራድ ሲሞክረው
- ኢትዮጵያዊው ‘ አይዞህ! ለመኾኑ አንተ የምርጫ ታዛቢ እንደመኾንህ ለአለቆችህ ተናግረሃል ወይ?
- ጣሊያን ‘ ምን ያደርጋል? እነርሱም የባለሥልጣኖቹ ደጋፊዎች ናቸው’ ማለቱን ወገናችን የኢጣሊያኑ በሽታ፥ በመጠኑም ቢኾን፥ በተጋባበት መልክ፥ ነግሮኝ “ አንተ በከንቱ ነው የምትለፋው@” ብሎ በቁጣ መልክ ገሰጸኝ። ለአንዳንዱ አገር ወገን፥ እንዲህ ባለበት ወቅትና ጊዜ አርፎ መቀመጥ ስለማይቻለው፥ የባሰ እንዳይመጣ ለመሞከር ይህን “የመተጋገዥያ ሃሳብ” አቀርባለሁ።

እስከዛሬ የድምጽ መስጫው ወረቀት የሚሰጠው መራጩ ሲመዘግብ እንደኾነ ተነግሮኛል። ይህም በወገን ላይ ያስከተለውን ጉድና ጉዳት ትቼ እሠለጠኑና በሕዝብ ድምጽ እሚሾሙ እሚሻሩበት አገር የሚሠራበትን ሥርዐት ላቅርብ።

## የምርጫ ድምጽ አሰጣጡ፥ አቆጣጠሩና አገላለጹ

፩- ለመምረጥ የሚያስችለው ማስረጃ
ይህ ማስረጃ በአኹኑ ጊዜ የሚሰጠው ለመምረጥ በተመዘገበበት ጣቢያ ነው። መኾን ያለበትም ነው

፪ የመምረጫው ወረቀት
የመምረጫው ወረቀት የሚሰጠውም እዚሁ መመዝገቢያው

ጣቢያ ነው። ይህ ግን ከስህተት አልፎ ወንጀል ነው። መምረጫው ወረቀት መሰጠት ያለበት ምርጫ ጣቢያው

ሲገባና ለመምረጥ የሚያስችለውን ማስረጃ ሲያቀርብ ብቻ ነው።
የመምረጫ ወረቀቱን የተቀበለ መራጭ በቀጥታ በምስጢር ድምጹን ወደሚሰጥበት ሳጥን በመሄድ ያለምንም ስጋት " አዩኝ-አላዩኝ" ብሎ ሳይሰቀቅ መብትና ግዴታውን ይወጣል።

፬- የምርጫው ሳጥን፦
ኹሉም ድምጽ የሚሰጠው አንድ ሳጥን ውስጥ ከኾነ ምርጫ ሰጭው ያለምንም ስጋት መስጠት ስለሚችል በመጋረጃም ኾነ በመከታ ሳይከለል ሊቀመጥ ይችላል። ምሥጢርነቱ ማንን እንደሚመርጥ ያለማሳወቁ ብቻ ነው እንጂ ወርቀቱን ተደብቆ መክተቱ ላይ አይደለም። በጸሐፊውም እይታ ይህ ከኹሉም የተሻለ ነው። በሚከተሉት ምክንያቶች፦
- መራጭ ምንም ዓይነት ሥጋት አይኖርበትም፦
- ተመልካች እገሌን መረጠ እገሊትን ለማለት መጨነቅ አይኖርበትም። ይዝናናል።
- ወጪም ይቀንሳል። መጋረጃ የለ መከታ ወይም የሳጥን ጋጋታ። እፎይ ጃል! የነፃነት ምልክት

፭- ድምጽ ቆጠራ።

- ድምጽ መቆጠር ያለበት ድምጽ በተሰጠበት ጣቢያ ብቻ ነው፦

፮- ድምጽ አቆጣጠር፦
- መጀመሪያ በድምጽ መስጫው ጣቢያ፦በምዝገባው መሠረት ድምጽ የሚሰጠውን መራጭ ቁጥር ተወዳዳሪዎች ተማምነውበት ይመዘገባል
- በጣቢያው ውስጥ የተሰጠው ድምጽ ይቆጠራል

- ተሰጠ የተባለው ድምጽ ከተመዘገበው መራጭ ቁጥር በላይ ከኾነ በቀጥታ ለገዥው የተሰጠው ድምጽ ውድቅ ይኾናል። ምነው? ቢሉ፣ ከገዥው በስተቀር ድምጽ መስጫውን ወረቀት ሊያገኝ የሚችል የለምና!
  ይህ የሚኾነው ግን የተሰጡት ድምጾች በየተወዳዳሪዎቹ ቁልል (ክምችት) ከተከፋፈለ በኋላ መኾን አለበት።አከፋፈሉ ልክ ለመኾኑ ጣቢያ ውስጥ ያሉት ማረጋገጥ አለባቸው።
- አኹን የድምጽ ወረቀቶቹ በተወዳዳሪዎቹ ስም ይለያል፦
- ይህ ትክክል መኾኑ ተወዳዳሪዎቹ በሚፈልጉት መልክ ይረጋገጥና ይቆጠራል።
- በዚህ ላይ ከላይ የተጠቀሱት በትክክል ለመፈጸማቸው ምርጫ ጣቢያው ውስጥ ያሉት ኹሉ መተማመኚያ ይፈርማሉ።
- እያንዳንዳቸውም የተፈረመውን ቅጂ ይይዛሉ።
- እያንዳንዱ ተወዳዳሪ ያገኘው ድምፅ ታሽጎ ከመተማመኚያው ቅጽ ቅጂ ጋር ወደ ምርጫ ቦርድ ይላካል/ይወሰዳል።

፯- የምርጫውን ውጤት አገላለጽ

ምርጫ ቦርድ፦

- ምርጫ ቦርድ ከምርጫ ጣቢያዎች ጋር ኹሉ የስልክ መገናኚያ ያመቻቻል።
- ለምርጫ ተሳታፊዎች መሪዎች ውይም ተወካዮች ምርጫ ቦርድ ውስጥ ወይም ሌላ አመቺ ሥፍራ ውጤቱን አብረው የሚሰሙበት ቦታ ያመቻችላቸዋል። ከየጣቢያው የሚመጣው ጥሪም ኾነ መልዕክት በድምጽ ማጉያ ለኹሉም መሰማት አለበት
  ይህም ገዢዎቹ የሚደርሳቸው የምርጫ መረጃ ለተወዳዳሪዎችም በእቻ መድረስ ስላለበት ነው።
  እንደ አሜሪካንና አውሮፓ ቢኾን ቅድመ ቴሌቪዥን በሬዲዮን ከዚያም  በተሌቪዥን ተወዳዳሪዎች ብቻ ሳይኾኑ መራጮችም እቤታቸው ኾነው ሊከታተሉት ይችሉ ነበር።ሕዝቡ ማን እንደሚገዛው ማወቅ ብቻ ሳይኾን ማን ከየት እንደተመረጠም ወዲያውኑ ቢሰማ እንደሚረካ አይጠረጠርም። መብቱም ነው።

ለሕዝብ ቢደበቅም ለተወዳደሩት መደበቅ ግን ፈጽሞ አይገባም ፍርሃት ካለ ግን …

፰- ምርጫ ጣቢያው ውስጥ የሚገኙት
- የምርጫ ቦርድ ወኪል
- ተወዳዳሪዎች
- የተወዳዳሪዎች የምርጫ ታዛቢዎች
- የምርጫ ታዛቢዎች ካገርም ኾነ ከውጪ

ሥነ-ሥርዐት አስከባሪ ከበር ውጪ መኾን አለበት ለአንዳንድ ጉዳይ በጥሪ ከሚገባበት ጊዜ በስተቀር።

፱- የሕዝቡን የመምረጥ መብቱን አሟልቶ ስለማክበር

- ምርጫ ምርጫ የሚኾነው የሩጫ እሽቅድምድም እንደሚደረግ ሲኾን ብቻ ነው።
ኃይሌ ገ.ሥላሴም ኾነ ጥሩነሽ ዲባባ ብቻቸውን ሮጠው ሊቀድሙ እንደማይችሉ፦ የሕዝብ ወኪልነትን ያለ ተወዳዳሪ መያዝ አይገባም አይቻልምም፡፤
እንዲህ ዓይነት ኹናቴ ሲደርስ፦ አኹን የምዝገባው ገደብ ስላለፈ ከምርጫው በኋላ ለመራጩም ለተመራጩም ዕድል ተሰጥቶ ከ…ወራት ባልበለጠ ጊዜ ምርጫው መደገሙ ይጠቅማል
- ሌላው በተለያዩ ምክንያቶች መራጮች ከቀረቡላቸው ተወዳደሪዎች መኻከል የተቀደሰ ውክልናን ለመስጠት ባይፈልጉ ይህ በግልጽ ተነግሯቸው ሌሎች ተወዳዳሪዎች በ… ወራት ውስጥ( እንደላይኛው) መፈጸም ይገባል።

ይህ ሊታወቅ የሚቻለው መራጮች መምረጫቸውን በአበላሹ ጊዜ ነው። የሚሻለው ግን “ የምመርጠው ይለኝም።” ይሚል

ዓይነት ነገር መምረጫው ላይ በጨመርበት ነው።

ይኽ ተፈጻሚነት ቢያገኝ የዘንድሮው ምርጫ ከቀድሞዎቹ በድምጽ አሰጣጡ ረገድ የተሻለ መብት የተከበረበት ይኾን ይመስለኛል።

ተፈጻሚነት እንዲያግኝም ለምርጫው ሥነ-ምግባር ደምብ ሕግ ኾኖ እንዲወጣ ከተደረገው ርብርቦሽና ትጋት የፈጠነና የተሟላ እንዲኾን ተወዳዳሪዎችን ኹሉ በወገን ስም አደራ። ነጠብጣቡን ከማስያዝ በላይ ልኼድ አልወደድኹም። ሞልተው የተረፉትን የሕግ ባለዎያዎች ልሻማ ካለመፈለግ በላይ አልችልምና!

ባታደርጉትስ፦

- ተቃዋሚዎች፦
  " የአህያ ባል ከጅብ አያስጥልም " ይባል ነበር። እናንተን ግን ' የዘንድሮ ተቃዋሚዎች የመራጮቻቸውን ኅይወትና ጤና በሕገ-መንግሥቱ መሠረት ከመጠበቅና ከማስጠበቅ ይልቅ የራሳቸውን... ፈላጊ ስለኾኑ አጋፍጠውሃልና...( አድርግ ብለን እስካሁን ባላያችሁት መንገድ ኹሉ ወገንን እንቀሰቅስባችኋለን።

- ከተቃዋሚዎች ውስጥ ለዚህ የሕዝብ ኅይወትና አካል ማዳን የማይተባበር ካለ ነጥለን በማጋለጥ ሕዝብ የሚያደርገውን እንዲያደርግ እናሳስበዋለን፦

- ገዥው ቡድን
  ምርጫ የሚባል ነገር ተጀመረ ከተባለበት ጊዜ ጀምሮ ሕዝብን ( ያደረገውን ኹሉ ለመዘርዘር ባይቻልም) ዋና ዋናውን እንኳን " ቁስላችንን እያከክን" አደባባይ አውጥተን "ሰውመሳይ በሸንጎ " በማለት የማንደርስበት መድረክ አይኖርም። የሞት - ሽረት ጉዳይ ነውና! ኢጣሊያኑ "...እነርሱም የሚደግፉት ባለሥልጣኖችን ነው " ያለው የትናንት ወግ ይኾናል

- የሃይማኖት መሪዎች፦
  የቀረበው ሃሳብ ፍትሐዊነትንና፣ ግልጽነትን፡- አቻነትንና ተአማኒነትን የያዘ በሕገ-መንግሥቱ ውስጥ ያለ በሕዝብ

ድምጽ ሥርዐት ውስጥ የሚተዳደር ኹሉ የሚያደርገው ስለኾነ እናንተ ቢቻል በኅብረት ኢትዮጵያ ውስጥ ያላችሁት ኹሉ፥ ባይቻል ለዚህ የተቀደሰ ተግባር ኹለቱም ወገኖች ተባብረው ተግባራዊ እንዲደርጉት ለዚህ ጎስቋላ ሕዝብ እንደምትደክሙለት ተስፋ አደርጋለሁ።

- ማንኛውም ወገን ባይቀበላችሁ የምታደርጉትን አድርጋችሁ ለሕዝቡ እንደምትነግሩት አልጠርጠርም።

- በደርግ ጊዜ ሙስሊም ወገኖቻችን የሕብረት ጸሎት በመጀመራቸው መላ ኢትዮጵያውያን ወገኖቻቸው ልብ እንደገቡ ናቸው።
- ምክራችሁን ባይቀበሏችሁ የኅብረት ጸሎትን እንደማይከለክሏችሁ ተስፋ አለኝ።

በውጪ አገር ያለነው ኢትዮጵያውያን ምርጫውን ደገፍን አልደገፍን እዚህ ላይ ቦታ የለውም። አገራችን ያለችበትን ኹናቴ እናውቃለን። ትርንጎን ሳንል ጫልቱን፤- ዘበርጋን ሳንል ኡመቾን ለወገን ቅድመ ቅንጅት እንደነበርነው ለመነሳት እንዘጋጅ

እግዚአብሔር ይርዳን

አሰፋ ሰይፉ